የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/0284/15
ቀን/Date 0 4 2015

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>ለግል መገልገያ እንዲውሉ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 923/2014 ስለመላክ፤</u>

የኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/1/2/908 ቀን 04/13/2014 በተጻፈ ደብዳቤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 33(2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የግል መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ አገር የሚገቡበት እና የሚወጡበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ማዘጋጀቱን እና መመሪያው በፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 16 መሠረት በፍትሕ ሚኒስቴር በኩል የተመዘገበ መሆኑን በመግለጽ መመሪያው በስራ ላይ እንዲውል የላከ መሆኑን አሳውቋል፡፡

በመሆኑም "ለግል መገልገያ እንዲውሉ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 923/2014" በጥንቃቄ ተፈጻሚ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ የገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያው ተፈጻሚ እንዲደረግ ያሳወቀበትን ደብዳቤ እና የመመሪያውን ቅጅ 09 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፤</u>
- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
- ለኮሚኒኬሽን የስራ ሂደት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለተቋማዊ ሥጋት ሥራ አመራርና ሥነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት
- ለሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለአምራችና ወጪ ንግድ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባና ሥሪት ሀገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለህግ ተገዥነትና ሥጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለሠው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>፤

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. 7/ኢ/1/21/908

ቀን / Date 04/13/2014

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 33(2) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የግል መገልገያ ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር የሚገቡበት እና የሚወጡበት ሁኔታ የሚወስን መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

መመሪያው በፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀፅ 16 መሠረት በፍትሕ ሚኒስቴር በኩል ተመዝግቧል፡፡

ስለዚህ መመሪያው በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እያሳሰብን ለአፈፃፀም እንዲረዳ መመሪያውን ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣

ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

ስልክ Letter Hub/GT
251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89

የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ

ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38

MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

# ለግል መገልገያ እንዲውሉ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

# ቁጥር 923/2014

Ethiopian Customs
Records & Docum

የገንዘብ ሚኒስቴር

ነሐሴ 2014

Ministry
ARCHIVE
2

# ለግል መገልገያ የሚውሉ ዕቃዎች ወደ አገር የሚገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 923/2014

የግል መገልገያ ዕቃዎች ወደአገር የሚገቡበትን ሁኔታ የሚወስነው በሥራ ላይ ያለው መመሪያ ለሕገ ወጥ ንግድ በር የከፈተ እና አገልግሎት አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደረ በመሆኑ ዓለምአቀፍ አሠራሮችን በተከተለ አኳኋን መመሪያውን አሻሽሎ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 እንደተሻሻለው) አንቀፅ 33(2) የግል መገልገያ ዕቃዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር የሚገቡበት እና ከአገር የሚወጡበትን ሁኔታ እንዲወስን ለገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ጠቅላላ ድንጋጌ

## ክፍል አንድ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ “ለግል መገልገያ እንዲውሉ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 923/2014” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጉም**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) “ለንግድ የማይውል ዕቃ” ማለት ጠቅላላ ብዛቱ በዚህ መመሪያ ከተወሰነው መጠን ያልበለጠ፤ ለባለመብቱ ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ ወይም ፍጆታ የሚውል ባለመብቱ ይዞት ወይም ከባለመብቱ ተለይቶ የሚመጣ ዕቃ ነው፡፡

   2) “የግል መገልገያ ዕቃ” ማለት ጠቅላላ ብዛቱ በዚህ መመሪያ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ፤ ለባለቤቱ ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ ወይም ፍጆታ እንዲውል በዚህ መመሪያ የተፈቀደለት ባለመብት ይዞት ወይም ከባለመብቱ ተለይቶ ወደአገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ዕቃ ነው፡፡

Ethiopian Customs Records & Docum...
Ministry of Finance ARCHIVES 2

3) “የስጦታ ዕቃ” ማለት ማንኛውም በውጭ አገር ያለ ሰው ወይም ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኝ ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ ጓደኛ ወይም ድርጅት የሚልከው የግል መገልገያ ዕቃ ነው፡፡

4) “መንገደኛ” ማለት ማንኛውም በየብስ ወይም በዓለምአቀፍ የአየር ማረፊያዎች በኩል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጣ ሰው ሲሆን በማጓጓዣው ላይ መደበኛ ሥራቸውን እየሰሩ ያሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሠራተኞችን እና ተመላላሽ ነጋዴዎችን አይጨምርም፡፡

5) “ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ” ማለት ከኢትዮጵያ ወጥቶ ከአንድ አመት ላላነሰ ጊዜ በውጭ አገር የሥራና የመኖሪያ ፍቃድ አግኝቶ ሲኖር የነበረ ወይም በስደት ውጭ አገር የቆየ ሆኖ ጓዙን ጠቅልሎ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

6) “የውጭ አገር ባለሙያ” ማለት በተለያዩ መንግሥታዊ መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ የልማት ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ዓለምአቀፍ፣ አህጉርአቀፍ ወይም አገር አቀፍ ድርጅቶች፣ ሕጋዊ ማህበራት፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግሥትና የግል የጋራ ድርጅቶች ውስጥ በሙያው ለማገልገል በሕጋዊ መንገድ ተቀጥሮ ወይም በሌላ ሕጋዊ ስምምነት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜጋ ነው፡፡

7) “ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ” ማለት በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ምዕራፍ 98 አወቃቀር ውስጥ ለተቀመጠው የዕቃ አይነት መግለጫ የተሰጠው ልዩ የታሪፍ መጣኔ ነው፡፡

8) “ከስደት ተመላሽ” ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ከኢትዮጵያ ወጥቶ በስደት የኖረና በመንግሥት ስምምነት ወይም ከነበረበት አገር ተገዶ ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

9) “ኮሚሽን” ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ነው፡፡

10) “ሚኒስቴር” ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡

11) “አዋጅ” ማለት የጉምሩክ አዋጅ ነው፡፡

12) በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

Ethiopian Customs Records & Docum... No.
Ministry of ARCHIVES 2 Finance

## ክፍል ሁለት

## ተፈላጊ ማስረጃዎች እና ለግል መገልገያ የሚፈቀዱ ዕቃዎች

3. **ማስረጃዎች**

ማንኛውም መንገደኛ፣ ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ፣ የውጭ አገር ባለሙያ እና የስጦታ ዕቃ ከውጭ አገር የተላከለት ሰው በዚህ መመሪያ የተመለከተው መብት ተጠቃሚ መሆን የሚችለው የሚከተሉትን ማስረጃዎች ሲያቀርብ ይሆናል፤

1/ **መንገደኛ፣**

ሀ) ፓስፖርት ወይም መንገደኛ መሆኑን የሚያሳይ ሌላ የጉዞ ሰነድ፣

ለ) በዚህ መመሪያ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር እንዲገባ ከተፈቀደው ውጭ ለሆኑ ዕቃዎች ዝርዝር መግለጫና የዋጋ ሰነድ፣

2/ **ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ**

ሀ) ፓስፖርት ወይም ሌላ የጉዞ ሰነድ፣

ለ) አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ውጭ አገር የኖረ መሆኑን የሚያሳይ ከአገር ሲወጣ እና ወደአገር ሲመለስ አግባብ ባለው የመንግሥት አካል በፓስፖርቱ ላይ የሰፈረ ማረጋገጫ ወይም በሚኖርበት አገር ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት የተሰጠና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማስረጃ፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በተገለፀው ቆይታ ወቅት መካከል ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ከዘጠና ቀናትና በላይ አገር ውስጥ ያልቆየ/ች ስለመሆኑ የሚቀርብ ማስረጃ፣

መ) የዕቃዎች ዝርዝርና ዋጋ መግለጫ፣

ሠ) ዕቃው አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ያገለገለ ስለመሆኑ በባለመብቱ የቀረበ ማረጋገጫ፣

ረ) ከስደት ተመላሾች ከስደት ተመላሽ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የቀረበ ማስረጃ፤

3/ **የውጭ አገር ባለሙያ**

አግባብ ካለው የመንግሥት፣ የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም አለምአቀፍ ተቋም ጋር ያደረገውን በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተረጋገጠ ውል፤

* Ethiopian Customs Records & Docum... ቁጥር No. 3
Ministry of Finance ARCHIVES 2

4/ <u>የስጦታ ዕቃ ከወጭ አገር የተላከለት ሰው</u>

ማንኛውም የኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ከውጭ አገር በስጦታ የመጣለትን የዕቃ ዝርዝር መግለጫ፣ የተላከውን ዕቃ ዋጋ ሰነድ፣ የመኖሪያ መታወቂያ እና የላከለትን ሰው ማንነት የሚገልጽ ማስረጃ፤

4. <u>ለግል መገልገያ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆነው የሚገቡ ዕቃዎች</u>

1/ ማንኛውም መንገደኛ የሚከተሉትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ለግል መገልገያነት ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፤

| ተ.ቁ. | የዕቃ ዝርዝር | መለኪያ | የሚፈቀደው መጠን |
|---|---|---|---|
| 1 | ሲጋራ | ግራም | 200 |
| 2 | ሲጋር | በቁጥር | 20 |
| 3 | ብትን ትንባሆ | ግራም | 250 |
| 4 | የአልኮል መጠጥ | ሊትር | 2 |
| 5 | ለሰላሳ ሽቶ | ሚሊ ሊትር | 500 |
| 6 | ሽቶ | ሚሊ ሊትር | 500 |
| 7 | ሞባይል | በቁጥር | 2 |
| 8 | ላፕቶፕ | በቁጥር | 1 |
| 9 | የፎቶ ግራፍ ካሜራ | በቁጥር | 1 |
| 10 | ዊልቸር | በቁጥር | 1 |
| 11 | የእጅ ሰዓት | በቁጥር | 1 |
| 12 | የጺም ወይም የጸጉር መላጫ | በቁጥር | 1 |
| 13 | የጸጉር ማድረቂያ | በቁጥር | 1 |
| 14 | የጸጉር መተኮሻ | በቁጥር | 1 |
| 15. | መንገደኛው የሚጠቀምባቸው መድሃኒቶች እና የህክምና መገልገያዎች | በቁጥር | ለአንድ ሰው በሚያስፈልግ መጠን |
| 16. | በጉዞ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ለቤተሰብ የሚያገለግሉ፤ልብሶች፤ጫማዎች እና የጽዳት እቃዎች | በቁጥር | ለአንድ ቤተሰብ ከሚያስፈልገው ያልበለጠ |



Ethiopian Customs Records & Docum... No
Ministry of ARCHIVES 2 Finance

2/ ማንኛውም ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ

ሀ) ተሽከርካሪን ሳይጨምር ቢያንስ ለአስራ ሁለት ወራት ሲገለገልባቸው የነበሩትን የግል መገልገያ ዕቃዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለመብቱ የሚያስመጣው የግል መገልገያ ኤሌክትሮኒክስ የሆነ እንደሆነ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር ማስገባት የሚችለው ከእያንዳንዱ የኤሌክትሮንስ ዓይነት አንድ ብቻ ነው፡፡

3/ ማንኛውም የግል መገልገያ ዕቃ በስጦታ የተላከለት ሰው፣

ሀ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሌለው ከሆነ ዕቃው ወደ አገር በሚገባበት ወቅት ሊከፈል ከሚገባው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በተጨማሪ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የሚሰላ 30 በመቶ የገቢ ግብር ይከፍላል፡፡

ለ) በስጦታ የሚላከለት ዕቃ ዋጋ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ መሰረት ከሆነው እስከ ማራገፊያ ወደብ ድረስ ካለው ዋጋ ( ሴ.ፍ.ኢ.ቢ.) ከ1000 የአሜሪካን ዶላር ሊበልጥ አይችልም፡፡

ሐ) በአንድ አመት ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ ስጦታ ሊቀበል አይችልም፡፡

4/ ለንግድ ዓላማ የማይውሉ ወደ ውጭ የሚላኩ ለግል ፍጆታ የሚውሉ የአገር ውስጥ ምርቶች የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡

## ክፍል ሶስት

## የግል መገልገያ ዕቃ የታሪፍ መጣኔ እና የዋጋ አተመመን

5. **ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ እና የዋጋ አተማመን**

1/ በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው በላይ ከመንገደኛ ጋር የሚመጡ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ሲሆን፣ ወጥ በሆነ የታሪፍ መጣኔ ቀረጥና ታክስ ይከፍልባቸው ይስተናገዳሉ፡፡

Ethiopian Customs Records & Documentation No

Ministry of ARCHIVES 2 Finance

2/ ለንግድ የማይውሉ ወደ አገር የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎች የቀረጥ መጣኔ በጉምሩክ ታሪፍ ምዕራፍ 98 መሠረት ይወሰናል፡፡

3/ ኮሚሽኑ ከአጠቃላይ የዋጋ አተማመን መርህ ጋር በማጣጣም ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች የቀረጥ ማስከፈያ መነሻ ዋጋ ያዘጋጃል፡፡

6. <u>ወጥ በሆነ የታሪፍ መጣኔ የማይስተናገዱ ዕቃዎች</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዕቃዎች ወጥ በሆነ የታሪፍ መጣኔ ሊስተናገዱ አይችሉም፤

1/ ባለመብቱ ለራሱ እና ለቤተሰቡ ጥቅም ላይ ሊያውለው ከሚችለው መጠን በላይ በተደጋጋሚ የሚያስመጣቸው በስጋት ሥራ አመራር ክትትል የተያዙ ዕቃዎች፣

2/ ለንግድ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎች፣

7. <u>የስጋት ሥራ አመራር</u>

1/ ኮሚሽኑ ወደ አገር ለሚገቡ ሰዎችና ዕቃዎች የሚሰጠውን ቀልጣፋ አገልግሎት እና በሂደቱ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ለማመጣጠን የሚያስችል ዓለምአቀፍ አሠራርን የተከተለ ዘመናዊ የስጋት ሥራ አመራርን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም ሲባል ሁሉም የአየር ትራንስፖርት አገልገሎት ሰጪ ድርጅቶች የመንገደኞችን ዝርዝር የሚገልፅ መረጃ አውሮፕላን ከማረፉ በፊት ለኮሚሽኑ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

3/ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለጉምሩክ ቁጥጥርና የስጋት ሥራ አመራር የሚያስፈልጉ መንገደኛን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማይሰጡ አጓጓዦች ላይ ከጉምሩክ ኮሚሽን በሚደርሰው መረጃ መሠረት እርምጃ ይወስዳል፡፡

Ethiopian Customs Records & Docum...
Ministry of ARCHIVES 2 Finance

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

8. ገደብ

1/ ማንኛውም ለንግድ ዓላማ የማይውል የግል መገልገያ ዕቃ ወደአገር የሚያስገባ ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ሰራተኛ የሚያስገባቸውን ዕቃዎች በሙሉ በአንድ ሰነድ አጠቃሎ ወደ ኢትዮጵያ በገባ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደአገር ማስገባት አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ባለመብት የግል መገልገያ ዕቃዎቹን በአየር መንገድ እና በየብስ አንድ ጊዜ የሚያስገባ ሆኖ ከሁለቱ የማስጫኛ ዘዴዎች በአንዱ ብቻ መጠቀም ከፈለገ በየብስ ወይም በአየር መንገድ ሁለት ጊዜ ብቻ ማስገባት አለበት፡፡ ሆኖም በዚህ መመሪያ በተፈቀደው መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

9. ክልከላ

ማንኛውም መንገደኛ በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው ውጪ የንግድ ዕቃዎችን ወደ አገር ማስገባት አይችልም፡፡

10. የተሻረ መመሪያ ወይም አሠራር

1/ የግል መገልገያ ዕቃዎች መመሪያ ቁጥር 51/2010 ከነማሻሻያው በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ አሠራርና ልማድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም ይህ መመሪያ በሌላ ሕግ መሠረት የተፈቀደን የግል መገልገያ ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት አያስቀርም፡፡

11. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ 23 ቀን 2014ዓ.ም

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር